# የሙሉዓለም ኢኮኖሚና የሉዓላዊነት ኢኮኖሚ

*መስፍን ወልደ ማርያም*

ሰኔ 2001

*ሪፖርተር* (ሰኔ 10፣ 2001) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምዕራባውያን በእርዳታ አሰጣጣቸው የአፍሪካን አገሮች የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት አያከብሩም በማለት ንግግር ማድረጉን ዘግቦል፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት (ከሦስት ዓመት የሚበልጥ አይመስለኝም) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሙሉዓለም (ግሎባል) ሌላ አማራጭ የለም ብሎ መናገሩ ትዝ ይለኛል፤ የሙሉዓለም ኢኮኖሚ ማለት የሉዓላዊነት ኢኮኖሚ ማለት ነው? ወይስ የሁለቱም ትርጉም በድንገት ተለወጠ? ለመሆኑ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ምን ማለት ነው; የሙሉዓለም ኢኮኖሚ ማለት ዓለም በሙሉ አንድ አምራችና አንድ ገበያ ማለት መስሎኝ ነበር፤ በአጠቃላይ ሲታይ የሉዓላዊነት ትርጉም ቀላል አይደለም፤ ከግለሰብ ዜጋ ይነሣል፤ ሉዓላዊነት ያላቸው ግለሰብ ዜጎች በአንድ ላይ የሕዝብን ሉዓላዊነት ይመሠርታሉ፤ የሕዝብ ሉዓላዊነት ከሀገረ መንግሥት ሉዓላዊነት ፍጹም የተለየ ነው፤ የሀገረ መንግሥት ሉዓላዊነት የጠመንጃ አገዛዝ ሉዓላዊነት ነው፤ በጭቆና አገዛዝ ስር ያለ ሕዝብ ሉዓላዊነት አለው ማለት ፌዝ ብቻ ነው፤ የሉዓላዊነት መሠረታዊውና ዋናው ትርጉሙ ከበላዩ ከሕግ በቀር ምንም ሌላ አዛዥ ኃይል የሌለው ማለት ነው፤ ምናልባት ከሁለት አገሮች በቀር በአፍሪካ ውስጥ የሕዝብ ሉዓላዊነት ብሎ ነገር የለም፤ ያለው የጠመንጃ አገዛዝ ሉዓላዊነት ነው።

በዓለም አጠቃላይ ኢኮኖሚ ደግሞ ጭራሹኑ ሉዓላዊነት ብሎ ነገር የለም፤ በግድ ምርትህን ልግዛህ፣ ወይም በግድ ምርቴን ልሸጥልህ የሚል የለም፤ በግድ ምርቴን በዚህ ዋጋ ግዛኝ፣ ወይም ምርትህን በግድ በዚህ ዋጋ ሸጥልኝ የሚል የለም፤ የኢኮኖሚ ባለሙያዎቹ የማይደፈርና የማይገሰስ የኢኮኖሚ ሕግ የሚሉት የአቅርቦትና የበገንዘብ የተደገፈ ተፈላጊነት ነው፤ ይህንን ሕግ ዱሮ በድንጋይ ዳቦ ጊዜ በጋማቤላ ገበያ አንዲት ሴት ዶሮዎች ትሸጣለች፤ አንድ ትንሽ ዶሮ ያዝሁና ስንት ነው ስላት ሃያ አምስት ሣንቲም አለችኝ፤ ትልቁን ዶሮ አነሣሁና የሄስ ስላት እሱም ሃያ አምስት ሣንቲም ነው ስትለኝ ገረመኝና ይሄ የዛችን ሁለት ያህላል እንዴት ዋጋቸው እኩል ይሆናል ብዬ በመደነቅ ስጠይቃት እየሳቀችብኝ ‹‹እኔ ሁለቱንም ዶሮዎች አልፈልጋቸውም፤ ልሸጣቸው ስለምፈልግ ለእኔ እኩል ናቸው፤ ምርጫ ያለህ አንተ ነህ፤ የሚያድግ ዶሮ ከፈለግህ ትንሹን፣ አርደህ የምትበላው ከፈለግህ ትልቁን ትገዛለህ፤›› አለችኝ፤ በእስዋ በኩል የዶሮዎቹ ዋጋ የሚወሰነው በኪሎ ሳይሆን ከዶሮዎቹ ሁሉ ለመገላገል ከመፈለግዋ የተነሣ ሁሉም እኩል በመሆናቸው ነው፤ በእኔ በኩል ደግሞ ከዶሮዎቹ ለመምረጥ ዋጋ የምሰጠው ዶሮዎቹን ለማርባት ወይም ለመብላት በአለኝ ፍላጎት ላይ ነው፤ አንዱ የማይፈልገውን ይሸጣል፤ ሌላው የሚፈልገውን ይገዛል፤ የገበያው ሕግ ይህ ነው።

አንድ የእንግሊዝ ፈላስፋ ንግድ ለሰው ልጅ ሥልጣኔ እድገት ያደረገውን አስተዋጽኦ ሲገልጸው ከዝርፊያ ወደዋጋ ክርክር መሸጋገር ነው ይላል፤ በገገርም ሆነ በሻጭ መሀከል ፈቃደኛነትና መግባባት በግድ አስፈላጊ ነው፤ ቢበዛም ‹‹የሚጥምህን አንተ ታውቃለህ!›› እንዳለው መንዜ አሽሙሩን ጥሎ መለያየት ነው።

የሚደንቀው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት እያለ የሚናገረው ስለእርዳታና ስለልማት መሆኑ ነው፤ ሁለት አስደናቂ ዓረፍተ ነገሮችን ብቻ ልጥቀስ፡--

‹‹***አፍሪካውያን የራሳቸውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዲያወጡ ዕድሉን ለሰጧቸው እንደሚገባ ተናግረዋል፤***›› ሁለተኛው አስደናቂ ዓረፍተ ነገር ደግሞ ይኸው፡-- ‹‹***የበለፀጉት አገራት ዕርዳታ ለመስጠት የአፍሪካ አገራት እነሱ የፈለጉትን ፖሊሲ ብቻ እንዲከተሉ ማስገደድ ማቆም እንዳለባቸውም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል፤***›› ሪፖርተርን ባምነውም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በትክክል የተናገረውን ስላልሰማሁ እነዚህን ዓረፍተ ነገሮች ብቻ ይዤ ብዙ ለመናገር አልፈልግም፤ ትክክልም አይሆንም፤ ሆኖም በአጭሩ ለመግለጽ የምፈልገው ከኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ተነሥቶ የራሳችንን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንድናወጣ ‹‹*ዕድሉን*›› ይስጡን ብሎ መለመን፣ ቀጥሎም እርዳታ ለመስጠት የበለፀጉት አገሮች በአፍሪካ አገሮች አመራር ላይ አስገዳጅ ተጽእኖ ማድረጋቸውን ማቆም አለባቸው ብሎ መማጸን የሚሉት ሀሳቦች እንዴት ነው አብረው የሚሄዱት? ሉዓላዊነትን የሚሻ የራሱን ተግባር ለመፈጸም ዕድል ስጡኝ ብሎ አይጠይቅም፤ ለሉዓላዊነት ዋጋ የሚሰጥ አታስገድዱኝ ብሎ በእጁ በያዘው ነገር አይማጸንም፤ ደግሞስ የምዕራባውያን ጥያቄ የአፍሪካን ሕዝብ ለመጥቀም እንጂ ለመጉዳት እንዳልሆነ ለምን በግልጽ አይነገርም? የሚሉት ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ ነው፤ የሚሉት የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ይረጋገጥ ነው፤ የሚሉት ሕጋዊ ሥርዓት ይኑር ነው፤ የሚሉት የአፍሪካ ሕዝብ ከጭቆና ቀንበር ይውጣ ነው፤ ታዲያ ክፋታቸው ምን ላይ ነው?

እርዳታ ተቀባይ ወይም በስሙ እንጥራው ካልን ለማኝ ሉዓላዊነቱ ከየት የመጣ ነው፤ አንድ ሰው ለመለመን አጎንብሶ እጁን ሲዘረጋ ሉዓላዊነት ተዘጋ፤ ምዕራባውያን አንድ አባባል አላቸው፤-- ለማኞች የተሰጣቸውን መቀበል እንጂ መምረጥ አይችሉም፤ ልመና የሉዓላዊነት ተቃራኒ ነው፤ ታዲያ በምን ተአምር ነው ለማኝ ሉዓላዊነቴን ተገፈፍሁ ብሎ የሚያማርረው? ምዕራባውያን የአፍሪካ ሕዝብ ሲራብ ለመመጽወት፣ የአፍሪካ አምባ ገነኖች ሲቸግራቸው ጠመንጃና ጥይት፣ ሎችም የጭቆና መሣሪያዎችን ለመመጽወት፣ ምን ግዴታ አለባቸው? እርግጥ እርዳታቸው ሁሉ በነጻ አይደለም፤ የሚከፈለው ግን በገንዘብ ሳይሆን በክብር፣ ያውም በአገር ክብር ነው።